# መልክዐ፡ቅዱስ፡ተክለሃይማኖት
# በአማርኛ



## ንዑድ ክቡር አባታችን ቅዱስ ተክለሃይማኖት

ተርጓሚ፡የደብረ ሊባኖስ አንድነት ገዳም

አዘጋጅ፡ ኪዳነ ማርያም

፩፤ ለፅንሰትከ፥ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
አስቀድሞ በማኅፀን ለተፀነስከው ፅንሰትህና በታኅሣሥ ሃያ
አራት ቀን ለተወለድከው መወለድም ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ሁሉ በሁሉ ዘንድ የተመሰገንህ ነህና እኔም
በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ
ብዬ እነሆ አዲሱን ምስጋናህን እጀምራለሁ፡፡

፪፤ ለዝክረ ስምከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
የስምህ የመነሻ ፊደሉ ትእምርተ መስቀል ለሆነው ሰም
አጠራርህ ሰላም እላለሁ፡፡ እሱም ገናናና የከበረ ስም ነዉ።

ቅዱስ አባት ሆይ!
የወንጌል ተቀዳሚ ስም ማቴዎስ የተባልክ አንተ ተክለ
ሃይማኖት ነህ እኮን ስለዚህም በችሎታዬ መጠን እንዳመሰግንህ
አንደበቴን ትፈታልኝ ዘንድ ድንግል ማርያምን እማልዳለሁ፡፡

፫፥ ለስእርተ ርእስከ፥ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
በአምላክ ኀሊና ለሚቆጠሩና ለሚታሰቡ የራስ ፀጉሮችህ ሰላም
እላለሁ፡፡ ይኸውም የክብር መጐናጸፊያ ያላቸው እንደ ሦስቱ
የይሁዳ ልጆች ናቸው፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
የቅዱስ ወንጌል ጸሐፊዋና ሰባኪዋ ማርቆስ የተባልክአንተ ተክለ
ሃይማኖት ነህ እኮን ስለዚህም ስለ ንጹሕ ወርቅና ብር ፈንታ
አባት ሆይ! የምስጋና እጅ መንሻ አቀርብልሃለሁ፡፡

፩! ለርእስከ፡ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
መልከ መልካሟ ሙሽራ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በንጹሕ የአፈር ወርቅ ለመሰለችው ርእስህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
የነፍስና የሥጋ ሐኪም ሉቃስ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህ እኮን፡፡ ስለዚህም ያን የገሃነመ ባሕረ እሳት ታሻግረኝ ዘንድ እኔ ምስኪኑ ልጅህ እታመንብሃለሁ፡፡

፪፤ ለገጽከ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ከፀሐይና ከጨረቃ ሥነ ጸዳል ይልቅ በክርስቶስ የምስጋና ሥነ ጸዳል ለተዋበው ፊትህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ትምህርትህ የተስፋፋ ትሩፋትህ የተትረፈረፈ ዮሐንስ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህ እኮን፡፡ ስለዚህ የዓለም ሥራው ብዙ ስለ ሆነ ንጹሑ የትእዛዝህ ቃል ከድካም ያሳርፈኝ፤ ከማዕሠረ ኃጢአትም ይፍታኝ፡፡

፫፣ ለቀራንብቲከ፣ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ሥነ ርእየታቸው የኩህል (ኩል) አምሳል ለሆነ ቀራንብትህ ሰላም እላለሁ፡፡ እሱ ለዓይኖችህ ግርማ ሞገስ እንዲሆኑ እነሱን ፈጥሮአቸዋልና፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ከሁሉ ይልቅ ሥልጣኑ ከፍ ያለ ጴጥሮስ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህ እኮን፡፡ መስቀልን የጦርመሣሪያ፣ ወንጌልን ጋሻ መከታ አድርገህ ጠላት ዲያብሎስን ድል ነሥተሃልና፡፡

፺፤ ለአዕይንቲከ! ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
በሥነ ተፈጥሮአቸው እንደ አጥቢያ ኮከብ ለሚያበሩ ዓይኖችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ከእንግዲህ አንተን ሞት ሊያገኝህ አይቻለውምና፡፡ እኔን አገልጋይህን ግድ ከሚል ከኃጢአት ሞት ሠውረኝ።

፺፩፤ ለአዕዛኒከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
በክብራን ነቢያት የተነገረውን፣ በቡሩካን ሐዋርያት የተሰበከውን፤ መልካሙን ምሣሌ ነገር ለሚያዳምጡ አዕዛኖችህ /ጆሮዎችህ/ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
በተፈጥሮ ጠባይህ ምድራዊ ሰው ስትሆን፤ በሥነ ምግባርህ ሰማያዊ መልአክ ነህና! ከልቅሶው፣ ከዋይታው በእሷ ዓርፍ ዘንድ፤ በወርቅና በዕንቍ በተሠራችው በሉዓላዊት ቤትህ ከዚህ ወስደህ አስቀምጠኝ።

፱፲ ለመላትሒከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
የማርያም ልጅ የፊቱን መጻፋት በማስብ በዐላውያን ጥፊ ሲጸፉ፣ /ሲጠፈጠፉ/ ላላፈሩና ላልፈሩ ጉንጮችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ሰማያዊ ዓርበኛ ሚናስ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህ እኮን፡፡ ስለዚህም ቅናትና፣ ምቀኝነትን፤ መከራንም ሁሉ ከኔ በማራቅ ዕውነትና ቅንነት ከአንደበቴ እንዲርቁ አታድርግ፡፡

፲! ለአእናፌከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
በድንግል ማርያም እና በልጅዋ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለ መዓዛ
መንፈስ ቅዱስን ለአሻተቱ አዕናፎችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
አኗኗርህ በብቸኝነትና በንጽሕና የሆነ ኤልያስ የተባልክ አንተ
ተክለ ሃይማኖት ነህና፤የጸሎትህ ኃይል የእሳት ነበልባል ሆና
አንዳችም ለወሬ ለዝና ሳታስተርፍ የኃጢአቴን እሾህ
ታቃጥልልኝ፡፡

፲፩! ለከናፍሪከ!ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ከምስጋና በቀር ከንቱ ነገርን ለማይናገሩ ከናፍሮችህ ሰላም
እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
አምልኮተ ጣዖት ጨለማን አስወግደህ በዓለም ላይየምታበራ
ፀሐይ አንተ መዓዛህ የተወደደ፤ ደብረ ከርቤን ነህ? ወይስ
መሠወር የማይቻላት ደብረ ጽጌን ነህን?

፲፪፤ ለአፉከ፤ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
የድንግል ማርያምን ልጅ ትምህርተ ወንጌሉን ዕውነተኛ
አምላክነቱን አምልቶ አስፍቶ ለሚያስተምር አፍህ ሰላም
እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
እንደ ደማስቆው ሐዋርያ ጳውሎስ ኢትዮጵያዊው ሐዋርያ
አንተ ነህ እኮን፡፡ ስለዚህም ቀድሞ በምስጋና እንደታወቁት
መዘምራን፤ አሳፍና ኤዶትም ዛሬም አንተን በመሰንቆ በበገና
ዝማሬ ላመሰግንህ እወዳለሁ፡፡

፲፫፤ ለአስናኒከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
በአፍህ ውሳጣዊ አካል እየወገን እየወገን እየወገናቸው ለበቀሉ ጥርሶችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
የቤተ ክርስቲያን የልጆቿ አባት ባስልዮስ የተባልክአንተ ተክለ ሃይማኖት ነህና አንተ ወዳለህበት ቦታ የላኳት ጸሎቴ እራቁቷን እንዳትገባ አንተ መልበሰ ተስፋ ሁናት፡፡

፲፬፤ ለልሳንከ! ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ንጉሡዋን ወይም ፈጣሪዋን የማርያምን ልጅ ታመሰግን ዘንድ ከልደትህ በሦስተኛው ቀን ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ለተሰጣት አንደበትህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
የቤተ ራባው ጸዋሚ ተሐራሚ ዮሐንስ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህና ያዕቆብ ላባን በየጊዜው ደስ እንዳሰኘው ሁሉ አንደበቴ አንተን ደስ ለማሰኘት የተዘጋጀች ናት፡፡

፲፭፤ ለቃልከ! ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
የአብ አካላዊ ቃሉ በሚሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሕዛብን ሁሉ ላሳመነ ቃልህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ! አንተ አባቴ ብርሃንህ የደመቀ ምሥራቃዊ ኮከብ ነህ ዓለምን በትምህርትህ የምታሞቅ ብሩህ ፀሐይ ነህ፡፡ ቂም በቀል ወይም ተንኮል የሌለብህ የዋህ ርግብ ነህ፡፡

፲፮! ለእስትንፋስከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ለሕሙማን ፈውስ፤ መድኃኒት የሚሆንና በተሰጠው ሥልጣንም ኃጢአትን ለሚያስተሠርይ እስትንፋስህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ለእግዚአብሔርመሥዋዕት ሆኖ የቀረበ ይስሐቅ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህ እኮን፡፡ ስለዚህም ለዚሁ ስም አጠራርህ የምስጋና ቃል ላበረክትልህ የተዘጋጀሁ ነኝ መስጠት ከማግኘት አንድ ነውና፡፡

፲፯1 ለጉርዔከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ባለ የሕይወት ዘመንህ ሩቡን ዘመን ውሃ ባለመጠጣትህ በውሃ ጥም ለተንጣጣው ጉረሮህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ጌታህ ኢየሱስ ክርስቶስ የጠፋ በግ አዳምን እንደፈለገው አንተም ብርቱ እረኛ ነህና፤ እኔን የጠፋሁትን በግ ፈልገህ ለማግኘት እሩጫህን አፋጥን፡፡

፲፰፤ ለክሣድከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
እንደ ወርቅ ሐብልና እንደ ዕንቊ ፈርጥ ቅናተ ዮሐንስን ለአጠለቀ ክሣድህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ዓለምን በትምህርትህ ያጣፈጥህ ጣፋጭ ጨው ነህ እኮን፡፡ ስለዚህም ከትምህርትህ ጣዕም የተነሣ ወንድ ልጅ ከአባቱ ተለይቶ፤ ሴት ልጅም ከእናቷ ተለይታ አንተን ለመከተል ይሽቀዳደማሉ፡፡

፲፱! ለመታክፍቲከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

የወንጌልን ቀንበር ለመሸከም፤ የመስቀልን መከራ ለመቀበል ፀጥ ለጥ ብለው ለፈጣሪያቸው ትእዛዝ ስተገዙ ትከሾችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
እሥረኛው የአርማንያው ጎርጎርዮስ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህና አባት ሆይ የልጆችህን መከራ ዓይኖችህ ይመልከቱ የዘመኑ ክፋትና ተንኰል አስጨንቋቸዋልና፡፡

፳! ለአክናፊከ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

በቀኝ ጎንህ ሦስት በግራ ጎንህ ሦስት ሆነው ሰሠረፁት ስድስቱ አክናፎችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
እኔ ልጅህ የአንተን በረከት እፈልጋለሁና የቀን ጉዳይ ጥሎኝ ለእርዳታ በምፈልግህ ጊዜ በነዚያ በክንፎችህ ፈጥነህ ድረስልኝ፡፡

፳፩! ለዘባንከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

በዕለተ ዓርብ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገረፈውን ግርፋት በማስብ ጽኑዕ ግርፋትን ለተገረፈ ዘባንህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

ቅዱስ ቁርባንን የምታቀርብ ንጹሕ ካህን እንደመሆንህ እኔን ለመርዳት ፈጥነህ ተነሣ አንተ ማድረግ የምትችለውን እኔ ለማወቅ አይቻለኝምና፡፡

፳፪፡ ለእንግድዓከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

የመንፈስ ቅዱስ ንጹሕ አዳራሽ በመሆን የጥበብ መገኛ ለሚሆን እንግድዓህ /ጀርባህ/ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

ግሙደ እግር ያዕቆብ ሐዋርያ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህ እኮን፡፡ ስለዚህም የእሳቱን ነበልባል በእጃቸው የሚዳስሱ ሰማያውያን መላእክት ስንኳ ሳይቀሩ ያደንቁሃል።

፳፫፣ ለክቡር ሕፅንከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

የባለሟልነትን ክብር ላከማቸህበት ክቡር ሕፅንህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

ባለ ዘመንህ ሁሉ፤ የሁሉ አምላክ ሁሉ ያንተ የሆነ ያለውም፤ የነበረውም ሁሉ በአንተ የሆነ ዕውነተኛ አምላክ አንተ ነህ ስትል ለድንግል ማሪያም ልጅ የመሰከርህ ዕውነተኛ ምስክር አንተ ነህ፡፡

፳፬፤ ለአእዳዊከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!በመላእክት ምስጋና የታጀበውን ፍጹም አምላክ የሆነ የማርያምን ልጅ ነበልባላዊ ምሥዋዕ ለዳስሱ እጆችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

እንግዳን መቀበል ፍጹም ተግባሩ የሆነ አብርሃም የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህና፡፡ የወይኑን አዝመራ ያለ ጊዜው ከሚያጭድ አጫጅ አድነኝ አባት ልጁን ያድን ዘንድ ግድ ነውና፡፡

፳፩! ለመዛርዒከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

ዓረማዊው ንጉሥ ወደገደል በወረወረህ ጊዜ ክንፍ ሆነው በዓየር ላይ ላንሳፈፉህ ክንዶችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

እኔን አገልጋይህን ጥለህ አትጣለኝ አንዲቷ ጸሎትህ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኃጢአቶቼን እንደ ጉም አብና እንደጢስ አትና ታጥፋቸው እንጂ፡፡

፳፪፣ ለኩርናዕከ፣ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

ሩጫህን በገድል፤ ትሩፋትህን በሥቃይ የፈጸምህ ለአዕዳወ ኩርናዕህ በኅብረት ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

ጸሐፌ ምሥጢራት፣ ወጥበባት ሄኖክ የተባልክ! መንፈሳዊ ጥበብን የተመላህ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህ እኮን፡፡ ስለዚህም ሁሉም አንደየሥራው ዋጋውን እስከ ሚያገኝበት ጊዜ ድረስ አንተ በክንፈ ረድኤትህ ጥላ ሥር ሸሽገህ አስቀምጠኝ፡፡

፳፯፤ ለእመትከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ የትዕግሥትንና የተጋድሎን ማኅደረ ሕንጻ መጥኖ ለከነዳ ክንድህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

ባሕሩን ያለመርከብ እንደምን ተሻገርከው? ተራራውንስ ያለገመድ እንደምን ወጣኸው? ይህም ድንቅ የጽድቅ ሥራህ በኔ ዘንድ ሲደነቅ ይኖራል፡፡

፳፯፣ ለእራኃቲከተክለ ሃይማኖት ሆይ!

ልዩ ትሩፋተ ሀብትን ለመስጠት እንደ ሁለት አክናፍ ለተዘረጉ መዳፎችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

መሥዕዋቱ የሠመረለት አቤል የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህ እኮን፡፡ አቤቱ ዘወትርበምትወጣበት ጊዜ በጠላቶቼ ላይ ክንድህን አንሣ፡፡ ይልቁንም ወደቤትህ በምትመለስበት ሰዓት ዕጥፍ በዕጥፍ በተቃዋሚዎቼ ላይ ኃይልህን ግለጽ፡፡

፳፱! ለአፃብዒከ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

ሥጋ መለኮትን ለሠዋና ደመ መለኮትን በዕርፈ መስቀል በጽዋ ለቀዳ ጣትህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

ለሰው ልጅ ዓለምን ቢነዳ፣ ቢገዛ ምን ይጠቅመዋል? እንደተባለው ከቶውንም አይጠቅመውምና፤ ሰውነቴን ወደ ንስሐ ጎዳና ምራት፡፡

፴! ለአጽፋሪከ ዘአዕዳው ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

እንደመልካም ሽቱ ልዩ መዓዛ ያላቸው ለእጆችህ አጽፋር ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
አንተ በዋሻ በነበርክበት ወራት የልጆችህን አዝመራ እንዳያጠፉ የዱር አራዊቶች በሥልጣነ ቃልህ የታሠሩ ሆኑ።

፴፩! ለገበዋቲከ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ወዲያና ወዲህ ተወጥረው በብረት ችንካር ተቸንክረው ለተወጉ ጎኖችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ሕዝብን የምታስተዳድር ዮሴፍ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህና፣ እኒያ ሰባቱ ጎዳናዎች ድካምን እንዳያመጠብኝ በዕረፍቴ ሰዓት ችግርን እንዳይፈጥሩብኝ ባለአደራነትህ ከኔ ከልጅህ አይለዩኝ፡፡

፴፪ ለከርሥከ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
የረኃብ ችግር ላልፈታው የቅባት ማጣት ላላደረቀው ሆድህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
እግዚአብሔርን በንጹሕ ልቡና የምታመሰግን ዳዊት የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህና ተግባራቸው ወይም ባሕላቸው ፀብ፤ ክርክር ከሆነ ሰዎች አድነኝ የዚህንም ዓለም ገዥ መልአክ ከፊቴ አሽቀንጥረህ ወዲያ አስወግደው፡፡

፴፫፤ ለልብከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
የማርያምን ልጅ የአምላክን ሕግ በትክክል የጠበቀ ቅዱስና ቡሩክ ለሚሆን ልቡናህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ፍጹም ዋጋቸውን ካገኙት ገባዕተ ሠርክ አንዱ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህና ሥራ ፈት ለሆንኩ ለእኔ አንተ ካገኘሃት ዋጋ የተረፈችውን ቅዱስ ሚካኤል ያሳትፈኝ ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልኝ፡፡

፴፬፣ ለኵልያቲከ፣ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
የብርሃናት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በትዕግሥት ለፈተናቸው ኵልያቶችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ስግደትህ በማዕረግ መላዕክት ደረጃ ነውና አከናውነህ የሠራሃት ጸሎትህ ባለ ዘመኔ ሁሉ ከጦርነት ከጽኑ መከራ ሁሉ ጠባቂ ትሁነኝ

፴፭፤ ለኀሊናከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ሳይጎድል፤ ትርፍ ሳይጨመር በሥላሴ ሦስትነት በትክክል ለሚያመልክ ኀሊናህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ከሐዲዎችን የምትበቀል ቄርሎስ የተባልክ አንተ ተክለሃይማኖት ነህ እኮን፡፡ አባት ሆይ! እኔን ልጅህን ፈጽመህ ባርከኝ ልጅን በመስቀል መባረክ ለመምህርየተለመደ ሕግ ነውና፡፡

፴፮፡ ለአማዑቲከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
በሰማይ በሚኖር በእግዚአብሔር አምላክ ፍቅርለተቃጠለው
አንጀትህ ሰላም እላላሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
አምላክህ የሰውን ልጅ ደኅንነት በአሰበ ጊዜ ፍቅርአገብሮት
አንዳች ኃጢአት ሳይኖርበት በፈቃዱ እንደሞተ፤አንተም ነፍሴ
የምትድንበትን መንገድ ፈልግ

፴፯፤ ለንዋየ ውስጥከ፤ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ለውስጣዊ ገንዘቦችህ ሁሉ በፍጹም ክብር ሰላም እላለሁ

ቅዱስ አባት ሆይ!
የሥላሴን አንድነት ሦስትነት በማስተማር ዓዋጅ ነጋሪነትህ
ፍጹም ድንቅ ነው፡፡ እባቡን በእርግጫ፤ አንበሳውን በጡጫ
ብለው የሚያልፉ የሴትና የወንድ ደቀ መዛሙርትን በጸጋ
ወልደሃልና፡፡

፴፰፤ ለሕንብርትከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ከናዝሬቱ ኢየሱስ ከማርያም ልጅ ደም የተዋሐደ በማዕከለ
ከርሥህ ለሚኖር ኅንብርትህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ከአረጋዊ ተክል የተገኘህ አዲስ የተክል አበባ ነህ። የሌዊና
የይሁዳ ካህናት ይህ ሰማያዊ መልአክ ነውን ወይስ ምድራዊ
ሰው፤ እያሉ እነሆ ስለአንተ ይደነቃሉ፡፡

፴፱፣ ለሐቋከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
በነቢይ ልማድ ወይም ባሕል የጽድቅን ቅናት ለታጠቀ ወገብህ ሰላምታ ይገባዋል እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ከታሠርኩበት የኃጢአት ሠንሠለት ፈጥነህ ፍታኝ፤ በምድር የፈታኸው በሰማይ የተፈታ እንዲሁም ያሠርከው በምድርም በሰማይም የታሠረ ይሆናልና፡፡

፵፤ ለአቍያጺከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
በዕብነ በረድ አዕማዶች ምሳሌ በወርቃማው ሥጋህ አቋም በየክፍሉ ለተሠሩ አቍያጾችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
የነገደ እሥራኤል አባት ያዕቆብ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህ እኮን፡፡ ጻድቅ ሰው ራሱ ድኖ ሌላውን ከመከራ ያድናልና፤ በልብህ ውስጥ እንደቀለበት አድርገህ አኑረኝ፡፡

፵፩፣ ለአብራኪከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ከላይ ከሰማይለወረደው ለእግዚአብሔር አምላክ ስግደትን ላዘወተሩ አብራኮችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
በኔ ላይ የተጫነውን ከባድ ሸክም አቅልልኝ!ከትእዛዞችህ አንዱን ስንኳ ጠብቄ ባልገኝም! አንተ ግን እንደ አባትነትህ ይቅርታ አድርገህ ልጄ ልጄ በለኝ።

፵፪፤ ለአእጋሪከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ! በባሕር መካከል ተሻግረው ወደ ኢየሱስ ሞዓ በደረሱ ጊዜ፤ክብርና ሞገስን ለተቀዳጁ እግሮችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
መሥዋዕተ ቍርባንን የምታሣርግ ከኪሩቤል እንደ አንዱ ነህና ፤ ከአንደበቴ የሚወጣውን ኃይለ ጸሎት አስበህ እኔ ኃጥኡ ያለንስሐ እንዳልቀሠፍ ጠብቀኝ።

፵፫፤ ለስኮናከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
በቁመት ብዛት እግርህ በመሠበሩ በደም ለተነከረ ሰኰናህ ሰለም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ትዕግሥትህ ፍጹም እንደ ኢዮብ ትዕግሥት ነው እኮን፡፡ አባት ሆይ! ኖኅ ልጆቹ ሴምንና ያፌትን እንደባረካቸው አንተም በዓለሙ ሁሉ ያሉ ልጆችህን /ደቀ መዛሙርትህን/ ባርካቸው፡፡

፵፬፤ ለመከየድከ፤ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
የማርያምንና የልጅዋን ሥነ ገጽ ለማየት ወደ ሃይማኖት ተራራ ለገሠገሡ የእግር ጫማዎችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
ዓየራዊ ንስር ገዳማዊ አንበሳ ነህና፤ የጦር አበጋዙ (አዛዡ) በኤልያስ ፊት ክብር እንደአገኘ የደብረ ሊባኖስ ክብረ ሞገሷ በፊትህ ክብር ይኑራት፡፡

፴፫፤ ለአፃብዒከ፤ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
በበገና አውታር ለተመሰሉ አሥሩ ጣቶችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
የጳውሎስ ደቀ መዝሙር ቲቶ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህና፤ በጎ ሥራህ /መልካምነትህ/ ያለዋጋ እንዳይቀርብኝ አቤቱ በደሌን አስወግደህ ይቅርታን አሰጠኝ ፡፡

፴፬፡ እንዘ ዕብል እገኒ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ስምንት ላይደሉ ዓሥር ለሚሆኑ አጽፋሮችህ /የእግርጣቶችህ/ ሰላም ፣ሰላም እያልሁ በንጹሕ ልቡና እጠራሃለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!
እንደ ሆሴዕና እንደዮፎኒ ልጅ እንደ ካሌብ ግብረ መልካም ነህና ከዚህ ከኃላፊው ዓለም  ፈልሼ በምመጣበት ጊዜ በክብር ተቀብለህ ወደሀገርህ መርተህ አስገባኝ፡፡

፴፺፤ ለቆምከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
አንደበቶች ሁሉ በሱ አማካይነት ምስጋና የሚያቀርቡበት ሰማያዊ መጐናጸፊያን ለተጐናጸፈ አካለ ቆምህ ሰላም እላለሁ፡፡
ቅዱስ አባት ሆይ!
የእግዚአብሔር የምስጋና አዳራሹ ጽኑዕ የምስሶ ዓምድ አንተ ነህና ኢያሱ ሙሴን እንደተከተለው አቤቱ አሠረ ፍኖትህን እከተል ዘንድ ወደአንተ ጥራኝ፡፡

፴፮፤ ለመልክአቲከ፤ተክለ ሃይማኖት ሆይ!
ያለአንዳች ልዩነትና ጉድለት በክርስቶስ አርአያ ለተመሰሉ መልኮችህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

ለሃይማኖቱ ቀናተኛ የሆነ የገሊላው ናትናኤል የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህና፤ በዓለም የታወቀችውን ሃይማኖትህን የራስ ወርቅ ትሆነኝ ዘንድ በራሴ ላይ

፶፱፤ ለፀዓተ ነፍስከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

ከዚች ዓለም የፈተናና የመከራ ቂም በቀል ኑሮ በመላእክት አጃቢነት በክብር ለተለየችው ፀዓተ ነፍስህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

የመርዓስ ዓቃቤ ሕግ ቶማስ የተባልክ አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህና በሕይወተ ሥጋ ሳሉ መታሰቢያህን ላደረጉ ሁሉ ጌታዬ ሆይ ክብርና ሞገስን አጎናጽፋቸው /ሠላምንና ፍቅርንም ስጣቸው።

፷፤ ለበድነ ሥጋከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

መዓዛው እጅግ ጣፋጭ በሆነ ሽቱ መምህር ኤልሳዕ ለገነዛት በድነ ሥጋህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

የጋዛው ፊልጶስ የተባልክ ሰባኬ ወንጌል አንተ ተክለ ሃይማኖት ነህና መሬታዊት ሥጋዬ ምድራዊ ህለውናዋ በተፈጸመ ጊዜ ስባረ ዓፅምህ መድኃኒት ይሁነኝ ሆኖ ይታዘዝልኝ።

፷፩፤ ለግንዘተ ሥጋከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

ደጋጎቹ የእስራኤል ነገሥታት በየጊዜውና በየዘመኑ ታላቅ አክብሮት በመስጠት ለሚማፀኑበት ግንዘት ሥጋህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

መሥዋዕትን የምታሣርግ ታላቅ ካህን የእግዚአብሔር ባለሟል ነህና ቀንዶቹ ዓሥር ከሆኑ ከዕባብ መተናኮልና አንደበቱ ሁለት ፊት ከሆነ ሰው ፀብ በክንፈ ረድኤትህ ሠውረህ አድነኝ፡፡

፶፪፤ ለመቃብሪከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

አንተ ከማረፍህ በፊት አስቀድሞ የድንግል ማርያምን ታቦት በክብር ለአስቀመጥክባት መካነ መቃብርህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

እኔን ድሀ አደግ ልጅህን የበረከትህ ረድኤት ከክፉ ሁሉ ይሠውረኝ፡፡ የጽድቅህ ጋሻ በሰማይና በምድር መከታ ይሁነኝ፡፡

፶፫፤ ሶበ አዕረፈ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

ከዚህ ዓለም ተድላ ደስታ ተገልሎ፤ ርቆ ረሀቡንና ውሀ ጥሙን ታግሦ፤ በዋሻ ውስጥ በዓረፈ ጊዜ፡፡

ይህን ቅዱስ አባት!

የማርያም መልክተኞች ቅዱሳን መላእክት ሊወስዱት ወደሱ መጥተው ፤ የዚህ ጻድቅ ሰው ሞት በእግዚአብሔር ፊት በዕውነት ክቡር ነው እያሉ በበገና ድምፅ ዘመሩለት፡፡

፶፬፤ ለፍልሰተ ሥጋከ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

ከገዳመ ዴላም ወገዳመ ደብረ ሊባኖስ ለፈለሰው ሥጋህ ሰላም እላለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

ስብከተ ወንጌልህ እንደቀድሞው ወንጌላዊ ማቴዎስ ስብከት ነው እኮን፡፡ አባት ሆይ፤ልጆችህ በዚህ ዓለም ብዙ መከራ ቢያገኛቸውም በአንተ ዘንድ ፍጹም ሰላምና ዕረፍትን እንዲሚያገኙ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ፡፡

፶፰፣ አኮ አኮ፣ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

ነገር በማብዛት ወይም በዝንጋታ ሳይሆን ፤ በድፍረት ያቀረብኩልህን ይህችን ጥቂት ምስጋና በታላቁ ጉባዔ ፊት ደስ ተሰኝተህ ተቀበል፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

እኔን አገልጋይህን እግዚአብሔር ከድቀትህ ትንሣኤን ይስጥህ የተከበረችና የተባረከች ድንግል ማርያምም ጽናቱንና ብርታቱን ታድልህ በለኝ፡፡

፶፱፤ እንዘ አኃሥሥ፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

በፍጹም ትጋት ሆነው እለ መርሐ ክርስቶስና ጴጥሮስ እንደፈለጉህ ሁሉ እኔም ያንተን በረከት ለማግኘት በመጣር ላይ እገኛለሁ፡፡

ቅዱስ አባት ሆይ!

ልመናዬን ትቀበለኝ ዘንድ በአጭር ቃል እለምንሃለሁ፤ ለጻድቅ ወይም ለዕውነተኛ ጥቂት ቃል ይበቃዋልና፡፡

፶፺፤ ስብሐት ይደልዋ ለማርያም፤ ተክለ ሃይማኖት ሆይ!

ያለቸልታና ያለዝምታ አንተን አመሰግንህ ዘንድ ዕድል ስለሰጠችኝ ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም በፍጹም ትጋት ስግደትና ምስጋና ይገባታል፡፡

**ቅዱስ አባት ሆይ!**

እነሆ መልክአ ጸሎትህን በምስጋና ተናግሬአለሁና፤ የሰጠኸኝንም ሥራ ሁሉ በሰላም ፈጽሜአለሁና አባት ሆይ ልቤን ደስ የሚያሰኘውን መልካሙን ሁሉ በተስማሚው መንገድ ፈጽምልኝ፡፡

፺፰፤ ለቀሚስከ፤ **ተክለ ሃይማኖት ሆይ!**

ለታጠቅኸው ቅናተ ዮሐንስና ለአጠለቅኸው መልበሰ ቀሚስህ፣እንዲሁም ለክቡሩ አጽፍህና ለራስህ አስኬማህ ሰላም እላለሁ፡፡

**ቅዱስ አባት ሆይ!**

ለእንጦንስና ለመቃርስ ልጆች መነኰሳት በሙሉ፤ በባሕርም፣ በየብስም ቢሆን አንተ **ተክለ ሃይማኖት** ክብራቸው፤ ሞገሳቸው ነህ እኮን፡፡

፺፱፤ ሰላም ለከ፤ **ተክለ ሃይማኖት ሆይ!**

ይህን ዓለም ንቀህ አጥቅተህ የወንጌልን ፍለጋ ተከትለህ በረኻ ለገባኸው፤ ለአንተ ሰላም እላለሁ፡፡

**ቅዱስ አባት ሆይ!**

መሥዋዕተ ቍርባንህ የምስጋና መሥዋዕትህ ከአቤል ይልቅ እጅግ የሠመረ ነውና፡፡ አባት ሆይ አባ አባ እያልኩ ስጠራህ ፈጥነህ ስማኝ በላይ በሰማይም አለሁልህ በለኝ፡፡

**አቤቱ የተክለ ሃይማኖት አምላክ ልዑል እግዚአብሔርሆይ!**

እኔን አገልጋይህን --------- ከክፉ ነገር ሁሉ ጠብቀኝ፤ቸርነትህ ለሁል ጊዜ አይለየኝ!

በመዓልትና በሌሊት፤ ቸር ጠባቂ መልአክ እዘዝልኝ፡፡

ለቅዱስህ ለተክለ ሃይማኖት በሰጠኸው ቃል ኪዳን ተማፅኜሀልሁና በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን አድለኝ፤ ከመከራ ሥጋ፤ ከመከራ ነፍስ ሠውረኝ ፤ ለዘላለሙ

አሜንወአሜን ለይኩን ለይኩን፡፡

ወድ ይህን መልክዕ አድራሽ ሆይ የዚህን መልክዕ አዘጋጅ ኃጥእ ኪዳነማርያምን በጸሎት ያስቡ ዘንድ ይለመናሉ!